# ምን ተዘጋጅቶልናል?

ሕዝብን ጨፍጫፊው የደርግ አገዛዝ ወደ ፍጻሜው ሲጓዝ ሀገር ወዳድ ሀይሎች ልዩነታቸውን ወደ ጎን ትተው ሀገርን ለማስቀደም በሚል ሊቀናጁ ሲነሱ ባእዳንና ገንጣዮች ደግሞ ውድቀትን አዘጋጅተውልን እንደነበር ኋላ በተከሰተው የገንጣዮች የበላይነት ልንገነዘብ ችለናል። ሀገር ወዳዶች ለህብረት ያደረጉትን ጥረት ወያኔና ወዳጆቹ የታገሉት፣ ሀገር ወዳድ ነን ይሉ የነበሩ ግን ቅጥረኛነታቸውን ለባዕድ ሀገር ባደረጉ ሀይሎች ተጠቅመው ነበር። ባዕዳኑ ከተከሰተው ገዳይ ረሃብ ጀርባ በወያኔና ሻዕቢያ ተጠቅመው እየተንቀሳቀሱ ስለነበር ይህን እቅዳቸውን የሚቃወም ሀገር ወዳድ ስብስብ መፈጠሩን በመጥፎ ገምተው ሊያከሽፉትም ጥረዋል።

የእሰቡትም በከፊል ተሳክቶላቸው የኢዴሐቅ ምስረታ ሊዘገይ ችሏል። ከተቋቋመም በኋላ የተወሰኑ ድርጅቶችን ደልለው ከወያኔ ጎን ሊያሰልፉም ችለዋል። በኤርትራ ግንጠላም ላይ ተስማምተው ነበርና--ተዘጋጅተውልን ነበርና--ይህን የሚደግፉና የወያኔን የከፋፍል ፖለቲካ የሚደግፉትን ሽግግር በሚሉት ጉባኤ እንዲገኙ አድርገው እነ አነግ ሳይቀር አጥፊያቸውን ስርየት አምጪ ብለው አጨብጭበው ተቀበሉት። የባዕድ ገንዘብ ብዙዎችን ህሊናቸውን ገደላላቸው፤ የህግርን ጥቅም አስረሳቸው። አክራሪ ሀገር ወዳድና ኢትዮጵያዊ የተባሉት ኢሕአፓና ኢዴሐቅ እንዲገለሉና እንዲጠቁ ተደርጎ ለወያኔ የበላይነት መንገዱ ተጠረገ፤ ተዘጋጅለት። ዛሬም መሰል ዝግጅቶች እየተደረጉልን ነው። ምን ተዘጋጅቶልናል ብሎ መጠየቅና ማወቅ ደግሞ የትግሉ ወሳኝ አካል ነው። የህገራችን ዕጣ ለባዕዳን ተሰጥቷልና የነገይቷን ኢትዮጵያ ቅርጽና ይዘት በተመለከተ በዋሺንግተንና ሎንዶን ያሉት ዕብሪተኞች ወሳኙ እኛ ነን ብለው እየተንቀስቀሱ ናቸው። መላ አፍሪካን በቁጥጥራቸው አስገብተውና ህብት ንብረቷንም ተቆጣጥረው (በተለይም ዘይት ቤንዚንን በተመለከተ) ሊግጡ ይፈልጋሉና ለአፍሪካ የሚቆሙ መሪዎችንና ድርጅቶችን አይፈልጉም። ከሉሙምባ፤ ንክሩማህ፤ ሞንድሊን፤ ሳሞራ ማሺል ጀምሮ የተነሱትን የአፍሪካ ጠበቆች ባዕዳኑ ገድለዋቸዋል። የራሳችንንም ሀገር ወዳዶች መጥቀስም እንችላለን። አፍሪቃን በነጻ ለመበዝበዝ አፍሪካን ማዳከምና ማበጣበጥም አላማቸው ነው። በአፍሪካ ውስጥ ገዝፈው ያሉ ሀገሮችን የመከፋፈል እቅዳቸው ለምሳሌ በሱዳንና በኢትዮጵያ ሰምሮላቸዋል። የምዕራቦቹ ጣልቃ ገብነት በአፍሪካና በተለይም በአካባቢያችን ይዞት ያለው ወይም የሚፈልገው ግብ ለአህጉራችንም ሆነ ለሀገራችን ጎጂ መሆናቸው የሚያጠራጥርም አይደለም።

ኢትዮጵያን በተመለከተ ባዕዳን ያዘጋጁልን የወያኔን ቅጥረኛ ቡድን በስልጣን ማስቀጠል ነው። አሊያም ሁኔታው ካስገደደ ደግሞ የወያኔን ቅጥረኛነት የሚቀጥል ተኪ ማዘጋጀት ነው። ይህ ሁሉ ከስራ ይውል

ዘንድ ደግሞ ትግል አፍራሽ የጦር ሀይል ከማዘጋጀት ባሻገር ሀገር ወዳድ ድርጅቶችን ማዳከምና ማጥፋት ተግባራቸው ሆኖ ይገኛል። ስለዚህም ባዕዳንም በወያኔ አፈና በቀጥታም በእጅ አዙርም ተካፋይ ናቸው። ወያኔ በበኩሉ የውስጥ ክፍፍሉና አውራጃዊነት ቢያምሰውም ሊሎችን በተመለከተና ሀገርን ከማዳከም አንጻር ግን የተባበረ ነው። ኢትዮጵያን ለማዳከም ደግሞ ጎጠኛነትን እያራገበና ሆዳም ከሀዲዎችን እየገዛ በዛው ልክ ጠላት ያለው ሕዝብ ላይ በከፋ ደረጃ ይዘምታል። በ አማራውና ሌሎችም ላይ እየደረሰ ያለውን ዘረኛ ጥቃት ያጤኗል። ሀገር ወዳድ ድርጅቶችን ማዳከም፤ መከፋፈልና የራሱን ቋንቋ ለመጠቀም ማምከን ደግሞ ብዙ መቶ ሚሊዮን ብር መድቦ እየሰራው ያለ ነው። ሁሉም ካልተሳካና የወያኔ አገዛዝ ውድመት አፍጦ ከመጣበት ደግሞ ወደ ትግራይ ፈርጥጦ ትግራይ ትግሪኝን ግንጠላ--በሌሎችም ግንጠላዎች ኢትዮጵያን አዳከሞ-- እውን ሊያደርግ ሊሞክር ዕቅድ አለው። ለዚህም ዝግጅቱን ከጀመረ፤ ትግራይን ማዘጋጀት ከጀመረ ጊዜ አልፏል። በአካባቢውም በባዕድ ቁጥጥር ስር ካሉ አገዛዞች ጋር ግንኙነቱን አጠናክሮ እንዳለ የሚታይ ነው። ለሱዳን አሳልፎ የሰጠው መሬት፤ ለጅቡቲ የሰጠው መሬት፤ ለቻይናና ለሌሎችም የሰጠው ሁሉ፤ የወሰደው የሀገርን ሉዓላዊነት ተጻራሪ እርምጃዎች ሁሉ ከውድቀት ያድኑት ዘንድ የተቃኙ፤ አሊያም ለክፉ ቀን የሚሆኑት ናቸው። ወያኔ ያዘጋጀልን የራሱን ቀጣይ የበላይነትና ካልሆነም የኢትዮጵያን ክፍፍልና ጥፋት ነው። እስከዚያው ግን ሀገሪቷን ጀግና አልባ ሊያደርጋት ተነስቷል። በዚህም ጥረቱ አውቀውም ሆነው ሳያውቁ እየረዱት ያሉ "ጠላቱቹ ነን ግን ..." የሚሉ ሀይሎች ወይም ዜጋዎች አሉ። ጥንቃቄ ሲያንስ ነው።

የቀድሞና አሁንም በትግል ያሉ ድርጅቶችን ተመክሮ በማጤን ስህተትን ከመድገም መቆጠብ ሲገባ ያንን እንደ አዲስ ሊሰሩ የሚታክቱና የሚደክሙ አሉ። ስለዚህም ስህተትን እየደገሙ ራሳቸውን መጉዳት ብቻ ሳይሆን በትግል ቆርጠው የተሰለፉትንም ያስጠቃሉ። በዘመነ ደርግ ኢሕዲአ ወይም ኢፒዴ የሚባል ቡድን አያሌ ኢትዮጵያዊ ዜጎችን በዝርክርክ አሰራር አጋልጦ ለሞት መዳረጉን እናስታውሳለን። ድርጅቶች ህይወቴን ለሀገሬ ልሰጥ ዝግጁ ነን ብለው የተነሱ ዜጎችን ሕይወት በንዝህላልነት ማጋለጥና ማስመታት የለባቸውም፤ ከባድም ስህተት ነው። ወያኔና ባእዳን በዚህ ድክመትና ስህተት ሊጠቀሙ ተዘጋጅተዋል። ያዘጋጁልን ወጥመድ ሀገር አድን ትግሉን ማምከንና ማፈን አላማው ያደረገ ነው። ወይ በያዙት ለመቀጠል ወይም ኢትዮጵያን ለመሰነጣጠቅና ለማጥፋት ነው -- ሌላ ግብ አላቸው የሚል ራሱን ያታልላል፣ ሕዝብን ያደናግራል። ዋናው ግባችንና ተልዕኮአችን ሀገራችንን ማዳን፤ የህዝባችንን ወሳኝነት ማስከበር ሆኖ ሳለ ወያኔ በየጊዜው ሌላ የትኩረት ጉዳይ እየፈጠርልን ሲያኳትነን ሲያባዝነን ቆይቷል። ለዚህም ተባባሪ ሆነው ራሳቸውን ተቃዋሚ ቢሉም "አብዮት አንሻም፤ ወያኔ ጠላት አይደለም፤ ኦባማዬ! አሜሪካንዬ!" የሚሉ ፍጡሮችም ይርመሰመሱብናል። የትግል አርአያና መሪ ሊሆን ቀርቶ በትግል ዙሪያ መገኘት የማይገባቸውን በስልት አሞግሰውም የትግሉ መሪ ብለን እንድንጮኽም ያደርጋሉ። መሪ ያላቸውም

ወዲያውኑ ሲከሽፉ፤ ለወያኔም ሲንበረከኩ፣ ያደነቃቸውና ደም መላሽ ይሆኑልናል ያለው ህዝብ ማፈር መሸማቀቅ ይገደዳል። ለ23 ዓመታት የቻልነው መከራ፤ የተቸከምነው ምጻት ይህ ነው። ታዲያ ነገስ ካለፈው ተምረን እንታረማለን ወይስ ዳግም መጫወቻ እንሆናለን? ለዚህ ህዝባዊ ምላሽ ያስፈለገናል።

ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል የሚለውን አባባል ሁኔታው ግድ ይላልና ስናርመው ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ የሚሰብር መስሎት ራሱን ይፈረካክሳል በሚል ባናርመው ተገቢ ነው። ላሉት ግዳጅ ሳይዘጋጁ ወሬን ሰንቀው የአፍ ጦርነት ለሚያደርጉት ወያኔ በቂ ምላሹን እንደሰጠ በተመከሮ አውቀናል። ስለ ትግል ሲወራና ሲደነፋ ግን በተጨባጭ በወያኔ ላይ ምንም ጥቃት ሳይደረግ በተስፋ ስንጠብቅ ዓመታት አልፈዋል። ዛሬም ቢሆን የሚያስፈልገን ይህን ልንፈጽም ነው ባዶ ጬኸትና ድንፋታ ሳይሆን የሚጠበቀውንና የሚፈለገውን ጥቃት በወያኔ ላይ ማድረሱ ነው። የፖለቲካው አለን ባዮችም የምላስ ጦረኞች ሆነው ከቀሩ መጨረሻችን አያምርም--ቀቢጾ ተስፋ ምሳችን ይሆናልና። ለዚህም ነው ከሚያወሩ ጋር ሳይሆን ከሚታገሉትና ከተግባር ሀይሎች ጎን መቆም ያለብን። ለዚህም ነው ስለ ትግል እያወሱ ከሚያነጉት ጋር ሳይሆ ሲታገሉ በተግባር መከራን ከሚቀበሉት ጋር እንሁን የምንውለው። ምነዋ የነ ሞት አይፈሬ ዘመን ያከተመ መሰለ? ምስጢር አውጥተን ሊሎችን ከማስጨረስ እንሰዋ ብለው ሞት ላይ የቀለዱት ጀግኖች ወኔ የት ገባ? ወኔ የእምነት ውጤት ነው። ለሀገራችን እንሰዋለን ብሎ የቆረጠ ዜጋ ለሀገሩ ህይወቱን የመስጠት ድፍረትን ይላበሳል። እምነት ካጠጠ ወይም ከተሸረሸረ ግን ትላንት ሞት አይፈሪ የነበረው ወንዝ ገብቶ ያልበዋል። ራሱን ማጥፊያ መርዝ ቢሰጠውም አይውጠውም፤ በጠላት ተይዞ ስየል ተቀብሎም ሆኖ ሳይቀበል የሚያውቀውን ሁሉ ለፍልፎ ሌሎችን ያስጨርሳል። ወያኔ በዚህ ድክመት ላይ ተስፋውን ጥሎ ያዘጋጀልንን የጥፋት ግብ ለማሟላት እየተዋደቀ ነውና ይህ እንዳይሟላ ለማድረግ ነቅተንና በጋራ ተሰባስበን እንታገል። የትግሉ ነው ህይወቴ፤ የሀገሬ ነው ህይወቴ ለማለትና ለማስመስከርም ብቃቱና ድፍረቱ ይኑረን።